የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
አዲስ አበባ–ሕዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5[th] Year No. 19
ADDIS ABABA – 8[th] Decem., 1998

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፮/፲፱፻፺፩ ዓ.ም
የግዥ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች
ምክር ቤት ደንብ ................................... ገጽ ፱፻፲፯

CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 46/1998
Procurement Services Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations ........................ Page 917

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፮/፲፱፻፺፩
## የግዥ አገልግሎት ድርጅት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯/፩/ /ሀ/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፩· አጭር ርእስ

ይህ ደንብ "የግዥ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፮/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· መቋቋም

፩· የግዥ አገልግሎት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ።

፪· ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል ።

፫· ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል ።

## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No. 46/1998*
## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF PROCUREMENT SERVICES ENTERPRISE (PSE)*

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47/1/(a) of the Public Enterprise Proclamation No.25/1992.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Procurement Services Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations No. 46/1998."

2. *Establishment*

1) The Procurement Services Enterprise (hereinafter "the Enterprise") is hereby established as a public enterprise.
2) The enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. *Supervising Authority*

A body to be designated by the Government shall be the supervising authority of the Enterprise.

